በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
Ministry of Education

**መመሪያ ቁጥር ፱፻፺/፪ሺ.፲፮**

**የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫ እና የአቻ ግመታ መመሪያ**

**Directive No 990/2024**

**Educational Credentials Authentication and Equivalency Directive**

**የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫ እና የአቻ ግመታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ**

በኢ..ፌ..ዲ..ሪ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የትምህርት ሚኒስቴር ይህ መመሪያ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**
**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

**፩. አጭር ርዕስ**
ይህ መመሪያ "የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫ እና አቻ ግመታ መመሪያ ቁጥር ፱፻፺/፪ሺ.፲፮ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**
የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 515/2014 እና የቴክኒክና ሙያ ስልጠና አዋጅ ቀጥር 954/2008 ላይ የተሰጡት ትርጓሜዎች እንዳሉ ሆነው በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም

***Educational Credentials Authentication and Equivalency Directive***

In accordance with artcle 19 sub article 4 of proclamation No1263/2021, by the powers and responsibilities of the FDRE executive bodies, the ministry of education declared this directive.

***Part one***
***General provisions***

1. ***Short title***

This directive shall be cited as "Educational Credentials Authentication and Equivalency directive number 990/2024"

2. ***Definitions***

Notwithstanding the definitions provided in Higher Education Proclamation No 1152/2019, Council of Ministers' Regulations No 515/2021 and Technical and Vocational Training Proclamation No 954/2016 unless the context requires otherwise, in this directive:

Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education

የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

፩/ **"ደንብ"** ማለት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 515/2014 ነው፤

፪/ **"የስልጠና ማስረጃ"** ማለት ከቴክኒክ እና ሙያ ስልጠና ተቋማት ስልጠናውን ስለማጠናቀቁ የተሰጠ ማረጋገጫ ማስረጃ ማለት ነው፤

፫/ **"ሰነድ"** ማለት የሙያ ፈቃድ ማስረጃ፣ የአቻ ግመታ ማስረጃ፣ የውክልና ሥልጣን መስጫ፤ ከፍ/ቤት የተሰጠ የስም ቅያሬ ማስረጃ እና ሌሎች ስልጣን ባለው አካል የተሰጡ ማስረጃዎችን ያካትታል፤

፬/ **"የትምህርት የጊዜ ምጣኔ"** ማለት ለአንድ የትምህርት መስክ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ስልጣን ባለው አካል የተመደበ ትምህርት የሚሰጥበት ሰዓት ነው፡፡

፭/ **"የተማሪው ቅጅ"** ማለት ተማሪው በተማረበት የትምህርት መስክ በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ እና በተቋሙ ወይም በስልጠና ማዕከሉ አካዳሚክ ሌጅስሌሽን የተካተቱትን ጉዳዩችን የያዘ ነው፡፡

፮/ **"ነፃ ሆነው የሚያዙ የትምህርት ዓይነቶች"** ማለት ተማሪው ቀደም ብሎ በተማረው የትምህርት መስክ የተማራቸውን የትምህርት አይነቶች

1/ **"Regulation"** shall mean the Regulation No 515/2022, issued by the Councils of Ministers to determine the structure, power and functions of the Education and Training Authority.

2/ **"Training Certificate"** shall mean certification issued to a trainer for completing training from technical and vocational institutions;

3/ **"Document"** shall mean unless otherwise given by the authority, which includes professional license, equivalency letter, power of attorney, name change issued by a court.

4/ **"Credit Hour"** shall mean a time period allotted by relevant authority to have sufficient time to deliver a certain field of study from beginning to end of the course;

5/ **"Transcript or Student Copy"** shall mean academic record of a student which incorporates affairs under harmonized educational policy and institutional or technical and vocational center academic legislations.

6/ **"Course Exemption"** shall mean a permit granted for a student not to take courses which were taken in a previous program of education when they appear at the next study;

7/ **"Equivalence Evaluation Certificate"** Shall mean a document the authority issues to the bearer of the certificate upon assessing the educational or training credential obtained

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

በሚቀጥለው የትምህርት መስክ ድጋሚ እንዳይማራቸው መፍቀድ ነው፤

፰/ **"የአቻ ግመታ የምዘና የምስክር ወረቀት"** ማለት ከውጭ ሀገር የተገኘ የትምህርት እና ስልጠና ማስረጃ በኢትዮጵያ የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ አውድ ውስጥ ተቃኝቶ አቻ ደረጃ የሚገልጽ በባለስልጣኑ ለትምህርት ማስረጃው ባለቤት የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

፱/ **"በበይነ-መረብ ትምህርት የተገኘ የትምህርት ማስረጃ"** ማለት ሙሉ በሙሉ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን በመጠቀም በበይነ መረብ አማካኝነት ተማሪ በአካል መገኘት ሳያስፈልገው ባለበት ቦታ ሆኖ ትምህርቱን በውጭ ሀገር ወይም ሀገር ውስጥ ካለ ተቋም በመማር የተገኘ የትምህርት ማስረጃ ነው።

፲/ **"የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ"** ማለት ከመጀመሪያ ዲግሪ በኃላ እና ከሁለተኛ ዲግሪ በፊት የሚሰጥየትምህርት ደረጃ ነው

፲/ **«ሰው»** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፩/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፤

፫. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

ይህ መመሪያ በሀገር ውስጥ ከሚገኙ የትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ለተገኙ

from foreign institutions as its equivalence is determined equal levels from the ones incorporated in the qualification framework of Ethiopia.

8/ **"Online Learning Educational Credential"** Shall mean a document obtained from a foreign or domestic higher education which offered entirely online using internet and ICT gadgets without the student being required to physically avail to the institutions.

9/ **"Post-Graduate Diploma"** shall mean educational qualification or certificate obtained by undertaking education or training between first and second degree.

10/ **"Person"** shall mean any natural person or an organ with legal personality.

11/ Any expressions in masculine shall include feminine expression as well.

3. ***<u>Scope of Application</u>***

This directive applies to persons seeking to authenticate or equivalence educational credentials obtained from local or foreign education and training institutions.

***<u>Part Two</u>***

***<u>Preconditions and Legal Documents Required for Authentication of Educational Credentials</u>***

4. ***<u>Preconditions Required to Authenticate Educational Credentials</u>***

1/ Unless otherwise a client shall fully complete and graduated, academic credentials shall not

የትምህርት ማስረጃ ለሚያረጋግጡ ወይም ከውጭ ሀገር ለተገኙ አቻ ግመታ ለሚሰራላቸው የትምህርት ማስረጃዎች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የትምህረት ማስረጃ ለማረጋገጥ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና አስፈላጊ ህጋዊ ሰነዶች

### ፬. የትምህረት ማስረጃ ለማረጋገጥ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

፩/ በባለስልጣኑ የትምህርት ማስረጃ ለማረጋገጥ የሚቀርብ ባለጉዳይ፤ የሚረጋገጥለትን ማስረጃ ትምህርቱን ጨርሶ የተመረቀ መሆን አለበት

፪/ የትምህርት ማስረጃ ሰነድ ለማረጋገጥ የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ መመሪያ በተመለከተው አግባብ መሰረት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፣

፫/ የአመልካቹ አስፈላጊ መረጃዎች በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የመረጃ ቋት ውስጥ አስቀድሞ በተገለፀው አግባብ መሰረት ገብቶ የሚገኝ መሆኑን አለበት፣

፬/ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የከፍተኛ ትምህርት የመግቢያ ሠርተፊኬት ማቅረብ

፭/ በሬጅስትራር ሀላፊ እና በአካዳሚክ

be authenticated by the authority

2/Application for authentication of educational credentials shall be submitted.

3/Applicant's mandatory information shall be filled in the authority's database.

4/ Higher education entrance certificate authenticated by the Education, Assessment and Examination Service shall be providing.

5/ Educational credential authenticated overleaf by the seal of issuing institution and duly signed and tittered by head of the registrar and academic dean or president shall be submitted

6/ The applicant's certificate front page shall contain the status of higher education which existed while the student was graduated and the transcript also contains the name of the institution, campus, modality, program, qualification, admission and graduation date (day, month and year) and the academic calendar within each semester or term.

7/ The applicant shall submit an evidence that verify pass the exit exam since it is implemented

8/ Any form of accademic credentials which has not been used as an admission requierement in any level of education shall not be acceptable for authentiction

9/ Authentication request through representative must include legal representation paper and identification card of the representative and

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ዲን ወይም ፕሬዚደንት ፊርማ እና ቲተር እንዲሁም በተቋሙ ማሕተም የኋላ ገጽ ላይ የተረጋገጠ የትምህርት ማስረጃ ማቅረብ

፪/ የትምህርት ማስረጃው የፊት ለፊት ገፅ ላይ የሰፈረው የተቋሙ ህጋዊ የደረጃ ስያሜ አመልካቹ በተመረቀበት ወቅት የነበረ እና በትራንስክሪፕቱ ውስጥ የተቋም ሰም፣ የካምፓስ ስም፣ ትምህርቱ የተሰጠበት መርሀ-ግብር፣ የትምህርት መስኩ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ትምህርቱ የተጀመረበትና ትምህርቱ የተመረቁበት ወቅት (ቀን፣ወርና ዓመተ ምህረት)፣ እያንዳንዱ ሴሚስተር ወይም ተርም የተሰጠበት ዓመተ ምህረት እና የትምህር ዘመን ማካተት አለበት፡፡

፫/ የመውጫ ፈተና ህግ ተግባራዊ ከሆነ ጊዜ ጀምሮ ተፈትኖ ያለፈ መሆኑን የሚገልጽ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፤

፬/ በማንኛውም የትምህርት ደረጃ ምዝገባ ወቅት ለመግቢያነት ያልቀረበ ወይም ያላገለገለ የትምህርት ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

፭/ በተወካይ በኩል ለሚቀርብ ጥያቄ ህጋዊ የውክልና ማስረጃ እና የተወካዩ መታወቂያ መኖሩን ማረጋገጥ እንዲሁም የስም ለውጥ ካለ የፍርድ ቤት ውሳኔ ማቅረብ አለበት፡፡

፭. <u>የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህረት ማስረጃ</u>

legal document from court if there is name change.

5. ***<u>Legal Documents Provided for Authentication of First Degree Educational Credentials</u>***

For the authentication of first degree educational credentials the applicant shall provide the following legl documents: these are:-

1/ First Degree Certificate and Transcript;

2/Matriculation result (High School Leaving Examination result) qualifying the minimum cut-off point to join higher education institution by the time the student was took the examination or joined higher education institution;

3/ The accademic result indicated on sub-article 2 of this article should be provided on a single paper

4/ If the high school completion certificate was obtained from a foreign institution, the person must obtain an equivalence evaluation certificate issued by the authority before starting their higher education.

5/ Graduates with old curriculum diplomas, 12+2 or 10+3 graduates, or level four graduates with technical, vocational, or education training must bring the original training certificate, diploma, and transcript that have been authorized by the authority, or from federal or regional technical,

**ለማረጋገጥ የሚቀርቡ ህጋዊ ሰነዶች**

የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ማስረጃ ለማረጋገጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ህጋዊ ሰነዶች መሟላት አለባቸው፡፡ እነዚህም፦

፩/ የመጀመሪያ ዲግሪ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት

፪/ አመልካቹ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በተፈተኑበት ዘመን ወይም የከፍተኛ ትምህርት በጀመረበት ወቅት የከፍተኛ ትምህርት የመግቢያ መቁረጫ ነጥብ የሚያሟላ ውጤት መግለጫ ሰርተፍኬት

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለፀው ውጤት በአንድ የውጤት ሰርተፊኬት የተገኘ መሆን አለበት፤

፬/ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ከውጭ ሀገር የተገኘ ከሆነ ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የተሰጠ የአቻ ግመታ የምዘና የምስክር ወረቀት

፭/ በቀድሞው ዲፕሎማ ወይም ከ12+2 ወይም ከ10+3 ወይም ከቴክኒክና ሙያ ደረጃ አራት ስልጠና ተመርቀው ያጠናቀቁ ትክክለኛነቱ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ወይም በፌደራል ወይም በክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም የተረጋገጠ ኦሪጅናል የስልጠና ማስረጃ ወይም ዲፕሎማ እና ትራንስክሪፕት፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ

vocational, or education training.

6/ The description stated under sub-article 5 of this article's must relate to the degree, previously acquired level four center of compence (CoC) and work experience included under the law.

7/ Regarding course exemption for first degree shall be as per the approved educational policy (legislation) and it includes..

A) Exempted Courses shall be clearly indicated on the transcript; while the service seeker appears to take the service, legal evidences shall be provided which entitled exemption of those courses;

B) Exemption of courses to which a score of less than "C" grade shall not be acceptable.

C) Graduates with old curriculum diplomas, 12+2 or 10+3 or level four graduates with technical, vocational, or education training and joined first degree prior to 2010 shall have their educational credentials to which courses were exempted from the above level of education be authenticated;

D) Course exemption emanated from institutions not licensed, dismissed for violating rules and regulation of the institution and from credentials which bear results below the passing grade

Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education

የተገለፀው ከዲግሪው ጋር ተዛማጅነት ያለው፤ ቀድሞ የተገኘ የደረጃ አራት የሙያ ምዘና እና በህግ የተደነገገው የስራ ልምድ

፯/ ኤግዘምሽን ኮርስ ኮርስ በተመለከተ ለመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት በሀገሪቷ የጸደቀው የትምህርት ፖሊሲ (ሌጅስሌሽን) የተቃኘ መሆኑ ያለበት ሲሆን፡-

ሀ) ኤግዘምሽን ኮርስ ኮርስ በትራንስክሪፕቱ ላይ በግልጽ መቀመጥ አለበት፤ ተገልጋዩ ለአገልግሎት በሚቀርብበት ወቅት ኤግዘምት የተደረጉ ኮርሶች የተወሰዱበት ህጋዊ ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፤

ለ) ከ ሲ (C) ውጤት በታች እንዲያዝ የተደረገ ኮርስ ተቀባይነት የለውም

ሐ) በቀድሞ ዲፕሎማ ወይም 12+2 ወይም 10+3 ወይም ደረጃ አራት ተምረው እስከ 2002 ድረስ የመጀመሪያ ዲግሪ የጀመሩ እና ከዲፕሎማቸው በመነሳት የተያዘ ኮርስ ያላቸው የትምህርት ማስረጃቸው ይረጋገጥላቸዋል፡፡

መ) ፈቃድ ከሌለው ተቋም፤ የተቋሙን የስነ ስርዓት ደንብ በመጣስ ከተባረረ፤ ከማለፊያ ነጥብ በታች የተገኘ ውጤት የትምህርት ማስረጃ ላይ ኤግዘምሽን ኮርስ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሠ) ተማሪው ለመመረቅ ከሚያበቃው አጠቃላይ ክሬዲት ሀወር ውስጥ 1/3ኛ

(academic dismissal) shall not be acceptable.

E) Course exemptions which go beyond 1/3 of the entire requirements for graduation shall not be accepted;

F) Only course exemptions made for similar course names and credit hours shall be accepted.

8/ Regarding transfer for first degree shall be as per the approved educational policy (legislation) and it includes...

A/ Credentials of Students requesting transfer from the institution closed upon the knowledge of the authority shall be accepted

B/ Educational credential of such a student is acceptable only if the student has taken over 50% of the credit hours required for graduation from the new institution;

C/ If a student seek to transfer to another institution to commence his studies in the new institution from where he stopped, such student should have finished at least one semester in the previous institution to proceed second semester in the new one;

6. ***Legal Documents Provided for Authentication of Master Degree Educational Credentials***

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

በላይ ኤግዚምሽን ኮርስ ተቀባይነት የለውም፡፡

ረ) ለተመሳሳይ የኮርስ ስያሜ እና ክሬዲት ሃወር ኤግዚምሽን ኮርስ ብቻ ተቀባይነት ይኖረዋል፤

፰/ ዝውውር በተመለከተ ለመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት በሀገሪቷ የጸደቀው የትምህርት ፖሊሲ (ሌጅስሌሽን) የተካተቱትን መሰረት አድርጎ የሚፈጸም ሲሆን ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል

ሀ) በባለስልጣኑ ታውቆ ከተዘጋ ተቋም የተዘዋወሩ ተማሪዎች የትምህርት ማስረጃቸው ተቀባይነት አለው፡፡

ለ) ተማሪው በራሱ ፈቃድ ወደ ሌላ ተቋም ከተዘዋወረና ለመመረቅ ከሚያበቃው አጠቃላይ ክሬዲት ሀወር ውስጥ ከ50% በላይ ከሚያስመርቀው ተቋም የተማረ ከሆነ የትምህርት ማስረጃው ተቀባይነት አለው ፡፡

ሐ) አንድ ተማሪ ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም በመዘዋወር ካቆመበት ለመቀጠል ቢፈልግ ከነበረበት ተቋም ቢያንስ አንድ ሴሚስተር ያጠናቀቀ ከሆነ ሁለተኛ ሴሚስተር ወደሚዘዋወርበት ተቋም መቀጠል ይችላል፤

**፯. <u>ድህረ-ምረቃ ዲግሪ የትምህርት ማስረጃ ለማረጋገጥ የሚቀርቡ ህጋዊ ሰነዶች</u>**

ድህረ-ምረቃ ዲግሪ የትምህርት ማስረጃ

To authenticate educational credential for masters degree the applicants shall be submit the following legal documents: these are:-

1/ Masters degree certificate and transcript; Shall provide evidence indicating that either the student has conducted Master's Thesis or is required to do such a research;

2/ First Degree Certificate and Transcript shall be provided and If the first degree was earned from a local higher education institution, the degree shall be authenticated by the authority pursuant to provisions of this directive or If the first degree was earned from a foreign higher education institution, equivalent letter of the degree shall be given by the authority;

3/ If there are bridge courses taken, the same shall be indicated on the transcript.

7. ***<u>Legal Documents Provided for Authentication of Doctoral Degree (PhD) Educational Credentials</u>***

To authenticate educational credential for doctoral degree the applicants shall be submit the following legal documents: these are:-

1/Third degree certificate and transcript;

2/ If the second degree was earned from a local higher education institution, the

ለማረጋገጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ህጋዊ ሰነዶች መሟላት አለባቸው። እነዚህም፡-

፩/ የሁለተኛ ዲግሪ የምስክር ወረቀት እና የተማሪ ቅጂ፣ የመመረቂያ ጽሁፍ የሰራ ወይም የመመረቂያ ጽሁፍ ለመመረቅ የማያስፈልገው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ መቅረብ አለበት፤

፪/ የመጀመሪያ ዲግሪ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት መቅረብ ያለበት ሆኖ፤ የመጀመሪያ ዲግሪው በሀገር ውስጥ ከሚገኝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተገኘ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተረጋገጠ መሆን አለበት ወይም የመጀመሪያ ዲግሪው ከውጭ ሀገር የተገኘ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አቻ ግምት የተሠራለት መሆን አለበት።

፫/ መሸጋገሪያ ኮርስ ካለ በትራንስክሪፕቱ ላይ በግልጽ መስፈር ይኖርበታል፤

፯. **<u>የሶስተኛ ዲግሪ የትምህረት ማስረጃ ለማረጋገጥ የሚቀርቡ ህጋዊ ሰነዶች</u>**

የሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ማስረጃ ለማረጋገጥ ከዚህ በታች የተገለጽት ህጋዊ ሰነዶች መሟላት አለባቸው። እነዚህም፡-

፩/ የሶስተኛ ዲግሪ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት

፪/ የድህረ-ምረቃ ዲግሪ የምስክር

degree shall be authenticated by the authority pursuant to provisions of this directive; or If the second degree was earned from a foreign higher education institution, equivalent of the degree shall be given by the authority;

*8.* ***<u>To Authenticate Educational Credential Earned by Cross Border Education;</u>***

Not-withstanding provisions of 6, 7 and this article, the following shall be fulfilled:

1/ The educational credential must have been issued by a foreign partner institution;

2/ Original educational credential and transcript signed and sealed overleaf by the foreign issuing institution as well as signature of head of the local partnering institution for true copy, shall be presented;

*9.* ***<u>Concerning Credential Authentication</u>***

1/ Applicants who were finalizing thier first degree untill August 2017 shall have authentications with out level four Center of competence (COC).

2/ Applicants who had commenced their degree program in 2015 should provide level four center of competence before finalizing their study

3/ As of 2017 Center of competence (COC) Certificates should be acquired prior to registration for degree program

4/ Admission to Technical and vocational institutions and higher education

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ወረቀትና ትራንስክሪፕት መቅረብ ያለበት ሆኖ የድህረ-ምረቃ ዲግሪው የምስክር ወረቀት በሀገር ውስጥ ከሚገኝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተገኘ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሊረጋገጥ ይገባዋል፤ ወይም የድህረ-ምረቃ ዲግሪው ከውጭ ሀገር የተገኘ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አቻ ግምት የተሠራለት መሆን አለበት፤

፰. **በድንበር ተሻጋሪ የተገኘ የትምህርት ማስረጃን ለማረጋገጥ**

ከላይ በአንቀጽ 6፣ 7 እና በዚህ አንቀፅ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ በታች የተገለፁት ሊሟሉ ይገባል።

፩/ የትምህርት ማስረጃው የተሰጠው ከውጭ ሀገር በመጣው ተቋም ሊሆን ይገባል፤

፪/ ከሰነዱ የኋላ ገጽ ላይ የትምህርት ማስረጃውን በውጭ ሀገር በሰጠው ተቋም ማህተም እና ፊርማ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ያለው ተቋም ከፍተኛ አመራር በማህተም እና ፊርማ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ኦሪጅናል የትምህርት ማስረጃ እና ትራንስክሪፕት መቅረብ ይኖርበታል።

፱.**መረጃ ማረጋገጥን በተመለከተ**

፩/ እስከ 2009 ዓ.ም መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን

institutions must be based on the cut-off point, which is determined annually by the appropriate authorized bodies. Aplicants who have acquired diploma in agriculture and teaching field and later pursued another degree program their credentials shall be approved ;

5/ Applicants who scored below 2.00 points in the old curriculum and graduated with a diploma in 12+2 or 10+3 in Technical and Vocational Education and Training fields and graduated with degree between 1999-2005 using the previous qualifications shall have their educational credentials authenticated;

6/ Educational credentials obtained by using matriculation results received from the old curriculum shall not be authenticated due to the fact that secondary school leaving examination results of the old curriculum may not be used to join degree program after 2008.

7/ Candidates who took higher education entrance examination in the new curriculum from 2004 through 2021 shall have their educational credentials authenticated by looking at fulfillment of the respective cut off points designated for the year the candidate had sitted for higher education entrance examination as well as a cut-off point fixed for one year shall serve for

ተምረው የጨረሱ ያለ ብቃት ምዘና ይረጋገጥላቸዋል፡፡

፯/ በ2008 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን የጀመሩ ዲግሪያቸውን ከማጠናቀቃቸው በፊት የደረጃ አራት የሙያ ምዘና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

፰/ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቶች ተማሪው የመጀመሪያ ዲግሪውን ለመማር ከመመዝገቡ በፊት የተጠናቀቁ መሆን አለባቸው፤

፱/ በግብርና እና መምህርነት ዲፕሎማ ተምረው በሌላ የትምህርት ዘርፍ ዲግሪያቸውን የጨረሱ የትምህርት ማስረጃቸው ይረጋገጥላቸዋል፡፡

፲/ በቀድሞው የ2ኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ውጤቱ ከ 2 ነጥብ በታች ሆኖ በዲፕሎማ /12+2/ እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና /10+3/ ገብተው ከ1991 ዓ.ም እስከ 1997 ዓ.ም ባሉት ጊዚያት ውስጥ ፈቃድ ካላቸው ተቋማት በያዙት ዲፕሎማ ዲግሪ ያጠናቀቁ ተማሪዎች የትምህርት ማስረጃቸው ይረጋገጥላቸዋል፡፡

፲፩/ ወደ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት እና ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመግቢያ መቁረጫ ነጥብ በተመለከተ ስልጣን ባለው አካል በየዓመቱ በሚወጡ የመቁረጫ ነጥብ አወሳሰን መሰረት

consecutive 5 years while candidates shall fulfill the cut-off point fixed for the respective year of examination by the time exam is taken as private candidate;

8/ Law graduates who are enrolled to degree program as of 2006 and passed exit examination shall have their educational credentials authenticated.

9/ Applicants who had started studies on health related disciplines in the evening or weekend programs till 2018 their documents will be authenticated.

## ***PART THREE***

## ***Preconditions and Legal Documents Required for Equivalence of Educational Credentials***

### ***10. Preconditions Required for Equivalence of Educational Credentials***

Evaluation for equivalence on educational credentials may be undertaken by the authority only while the following preconditions shall fulfill:

1/ Application for equivalence of educational credentials shall be submitted.

2/ Where the educational and training credential to be evaluated bears authentication seal of ministry of foreign affairs of the issuing country, that of Ethiopian Embassy as well as Ministry of Foreign Affairs of Ethiopia for authenticity, where the certificate has no erasure or

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ይሆናል፡፡ እስከ 2000 ዓ.ም በቀድሞው የትምህርት ፖሊሲ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ውጤት ዲግሪ ተምረው ያጠናቀቁ ተማሪዎች የትምህርት ማስረጃቸው ይረጋገጥላቸዋል፡፡ ነገር ግን ከመስከረም 2001 ዓ.ም ጀምሮ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ውጤት አወሳሰን ይሆናል፡፡

፯/ ከ1996 ዓ.ም እስከ 2013 ዓ.ም በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ተምረው ፈተና በተፈተኑበት ዘመን ወይም የከፍተኛ ትምህርት በጀመሩበት ወቅት የመግቢያ መቁረጫ ነጥብ የሚያሟሉ የትምህርት ማስረጃቸው ይረጋገጥላቸዋል፡፡ እንዲሁም በ2014 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ዘመን የተቆረጠ የመግቢያ ነጥብ ለ5 ተከታታይ ዓመታት የሚያገለግል ሲሆን ከ5 ዓመታት በኋላ ግን በግል ተፈትነው በዘመኑ የሚቆረጠውን የመግቢያ ነጥብ ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

፰/ ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ በህግ ትምህርት ዲግሪ የጀመሩ የህግ መውጫ ፈተና የወሰዱና ማለፊያ ነጥብ ያመጡ መሆን አለባቸው፡፡

፱/ ከ2010 ዓ.ም ድረስ በማታ ወይም በቅዳሜና እሁድ በጤና የትምህርት መስኮች ትምህርት ጀምረው የተመረቁ የትምህርት ማስረጃ ይረጋገጣል፡፡

cancellation and wordings clear and legible to read and contents bear no self-contradiction;

3/ The applicant shall present passport, visa or residence permit or related legal documents showing his or her presence in the country of origin during the training period.

4/ Where the service seeker is a foreign citizen, such person shall bear legal documents

5/ The foreign institution which issued the educational or training credential shall have an accreditation to educate or train in the field of education or training the certificate has been issued.

6/ Where there is transfer of students or trainees from a foreign institution to a local education and training institution, it shall be allowed by the authority while technical issues are determined according to the senate legislation of the institution;

7/ Where the country from which the educational credential is obtained has qualification framework, the qualification level of the certificate shall be determined by comparing it with the Ethiopian qualification framework;

8/ Where the country from which the educational credential is obtained has no qualification framework, the qualification level of the certificate shall be determined by

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Education

## ክፍል ሶስት

## አቻ ግመታ አገልግሎት ለማከናወን የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች እና ህጋዊ ሰነዶች

### ፲. አቻ ግመታ አገልግሎት ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ለምዘና የቀረበው የትምህርት እና ስልጠና ማስረጃ ከባለስልጣኑ የምዘና ሰርተፊኬት የሚሰጠው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟለቶ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

፩/ የአቻ ግመታ አገልግሎት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ፡፡

፪/ የቀረበው የትምህርት እና ስልጠና ማስረጃው በተገኘበት ሀገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ኤምባሲ እንዲሁም በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትክክለኛቱ የተረጋገጠ፤ ስርዝ ድልዝ የሌለበት፤ ፊደላቱ በጉልህ ለመለየት የማያስቸግር፤ በይዘቱ እርስ በርሱ የማይጣረስ ከሆነ

፫/ በተማረበት ሀገር ለትምህርት የቆየበትን ጊዜ የሚያሳይ ፓስፖርት፤ ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፍቃድ ወይም ተዛማጅ ማስረጃ ማቅረብ

፬/ አገልግሎት ፈላጊው የውጭ ዜጋ ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ህጋዊ ሰነድ ማቅረብ አለበት

፭/ የትምህርት እና ስልጠና ማስረጃውን የሰጠው የውጭ ሀገር ተቋም የከፍተኛ

comparing the curriculum of the issuing foreign institution with the Ethiopian qualification framework;

9/ Where the educational credential was obtained prior to the period in which qualification framework was designed, the equivalence level of the certificate shall be determined by comparing the curriculum of the issuing foreign institution with that of Ethiopia;

10/ Where the educational credential presented for equivalence evaluation has no clear reference on the qualification framework of the issuing country while it fulfills the above other criteria set in this directive, decision may be made based on the Ethiopian qualification framework

11/ Where it is difficult to get sufficient information required for offering the service, the authority may request such information from concerned foreign institutions or embassies and consulate offices to provide such additional information the authority requires.

12/ Request for equivlence through representative must include legal representation paper and identification card of the representative and legal document from court if there is name change

### *11. For applicants who completed Secondary School study abroad and seek to pursue*

ትምህርት ለማስተማር የተቋም ወይም የትምህርት መስክ በተማረበት መርሃ ግብር እውቅና ያለው መሆን ይገባዋል፡፡

፪/ በውጭ ሀገራት ከሚገኙ የትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ወደ ሀገር ውስጥ የትምህርት እና ስልጠና ተቋማት የሚደረጉ የተማሪዎች ወይም ሰልጣኞች ዝውውር ሲኖር የትምህርት ማስረጃው በባለስልጣኑ አቻ ግመታ የሚሰራለት ሆኖ ቴክኒካል ጉዳዮች ግን በተቋማት ሴኔት መተዳደሪያ ህገ ደንብ መሰረት ይወሰናል፡፡

፫/ የትምህርት እና ስልጠና ማስረጃው የተገኘበት ሀገር የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ካለው ከኢትዮጵያ የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ጋር በማነፃፀር ለምዘና የቀረበው ማስረጃ ደረጃ ይወሰናል፡፡

፬/ የትምህርት እና ስልጠና ማስረጃው የተገኘበት ሀገር የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ከሌለው የሀገሪቱን የትምህርት ስርዓት ከኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓት እና የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ጋር በማነፃፀር ለምዘና የቀረበው ማስረጃ ደረጃ ይወሰናል፡፡

፭/ ለምዘና የቀረበው የትምህርት እና ስልጠና ማስረጃ የተገኘበት ዘመን ማስረጃው የተገኘበት ሀገር የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ ከማዘጋጀቱ በፊት

***first degree locally shall require the following legal documents:***

In addition to the requirements listed under article 10, the following shall be fullfiled,

1/ Secondary School Certificate or Diploma credential

2/ High school completion certificate or diploma of the candidate must have met the cut-off point for entrance into higher education institution as per the standard of issuing country;

3/ Where the educational credential of the applicant is obtained from a curriculum of a country different from the one he/she had attended schooling, entrance point shall be determined as per the cut-off point of the country where he had obtained the certificate;

4/ Where the applicant attended an international or community school accredited by the Ethiopian Government, support letter is required from the school;

12. ***For those who studied associate degree abroad and seek to pursue first degree locally:***

In addition to the requirements listed under article 10, the following shall be fullfiled,

1/ Associate degree certificate and transcript

2/ Where the secondary school completion certificate is obtained from Ethiopia, the certificate shall be authenticated by the

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ከሆነ የሀገሪቱን የትምህርት ስርዓት ከኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓት ጋር በማነፃፀር ደረጃ ይሰጠዋል፡፡

፲/ ለምዘና የቀረበው የትምህርት እና ስልጠና ማስረጃ በተገኘበት ሀገር የትምህርት ስርዓት ውስጥ ቦታው ወይም ደረጃው በግልፅ የማይታወቅ ከሆነ፤ነገር ግን በዚህ መመሪያ ከላይ የተዘረዘሩትን ካሟላ የኢትዮጵያ የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍን መሰረት በማድረግ ውሳኔ ይሰጠዋል፡፡

፲፩/ አገልግሎቱን ለመስጠት በቂ የሆነ መረጃ ማግኘት ካልተቻለ ባለሥልጣኑ የሚመለከታቸውን የውጭ ሀገራት ተቋማት ወይም ኤምባሲዎች ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ተጨማሪ መረጃ እንዲሰጡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፲፪/ በተወካይ በኩል ለሚቀርብ ጥያቄ ህጋዊ የውክልና ማስረጃ እና የተወካዩ መታወቂያ መኖሩን ማረጋገጥ እንዲሁም የስም ለውጥ ካለ የፍርድ ቤት ውሳኔ ማቅረብ አለበት፡፡

፲፫. <u>ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በውጭ ሀገር ተምረው የመጀመሪያ ዲግሪ በሀገር ውስጥ መማር ለሚፈልጉ ማቅረብ ያለባቸው ህጋዊ ሰነዶች</u>

ከላይ በአንቀጽ ፲ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው

Ethiopian examination and assessment service

3/ Where the secondary school completion certificate is obtained from foreign country, the authority may assess according to this directive;

13. ***Applicants pursue equivalence of educational credentials obtained first degree abroad and would like to work or study in Ethiopia:***

In addition to the requirements listed under article 10, the following shall be fullfiled,

1/ First degree and transcript;

2/ Secondary School Completion certificate authenticated by the educational examination and assessment service;

3/ Where the secondary school completion certificate is obtained from foreign country, the authority may assess according to this directive;

4/ If the applicant had used diploma as entry for first degree, the diploma should be obtained from accredited institution and original diploma and transcript must be authenticated;

14. ***Applicants pursue equivalence of educational credentials obtained Master degree abroad and would like to work or study in Ethiopia:***

In addition to the requirements listed under article 10, the following shall be fullfiled,

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፦

፩/ የሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ወይም ዲፕሎማ፤

፪/ ማስረጃው በተገኘበት ሀገር የዲግሪ የትምህርት መስክ ለመከታተል የሚያስችል የማለፊያ ውጤት ያለው የሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ወይም ዲፕሎማ እና ትራንስክሪፕት፤

፫/ የአመልካቹ የትምህርት ማስረጃ ትምህርቱን ከተከታተለበት ሀገር ስርዓተ ትምህርት ውጪ በሌላ ሀገር ስርዓተ ትምህርት መሠረት ከሆነ የመግቢያ ውጤቱ የሚወሰነው አመልካቹ ትምህርቱን በተከታተለበት የትምህርት ስርዓት ውጤት አወሳሰን መሠረት ይሆናል፤

፬/ አመልካቹ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ እና የኢትዮጵያ መንግስት ፈቃድ በሰጠው ዓለም አቀፍ ወይም ማህበረሰብ ትምህርት ቤት የተማረ ከሆነ ከትምህርት ቤቱ የድጋፍ ደብዳቤ ያቀርባል፡፡

**፲፪. <u>አሶሼት ዲግሪ በውጭ ሀገር ተምረው የመጀመሪያ ዲግሪ በሀገር ውስጥ ለመማር አመልካቾች የሚያቀርቡት ህጋዊ ሰነዶች</u>**

ከላይ በአንቀጽ ፲ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ማሟላት

1/ Second degree and transcript

2/ First degree certificate and transcript

3/ Where the first degree was obtained from a locally higher education institution, the authority may authenticate it according to this directive;

4/ Where the first degree was obtained from foreign country, the authority may evaluate the credentials according to this directive;

***15. <u>Applicants pursue equivalence of educational credentials obtained Doctoral degree abroad and would like to work in Ethiopia:</u>***

In addition to the requirements listed under article 10, the following shall be fullfiled,

1/ Third degree certificate and transcript

2/ Proof of PhD dissertation produced;

3/ Second degree and transcript

4/ Where the first and second degrees were obtained from local higher educatin institutions, the authority may authenticate it according to this directive;

5/ Where the first and second degrees were obtained from foreign country, the authority may evaluate the credentials according to this directive;

6/ Where the academic credential fails to clearly indicate the field of study apart from the title of dissertation (thesis), additional documents for evidence shall be presented;

***16. <u>To undertake equivalency for</u>***

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ይጠበቅባቸዋል

፩/ የአሶሼት ዲግሪ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት፤

፪/ የሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ከሀገር ውስጥ የተገኘ ከሆነ በትምህርት ምዘና እና ፈተናዎች አገልግሎት ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ሰነድ

፫/ የሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ከውጭ ሀገር የተገኘ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት በባለስልጣኑ የተመዘነ መሆን አለበት።

፲፫.<u>የመጀመሪያ ዲግሪ ኖሯቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀጥሮ ለመስራት ወይም ለመማር የሚያገለግል ምዘና ለማሠራት</u>

ከላይ በአንቀጽ ፲ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ማማሏት ይጠበቅባቸዋል

፩/ የመጀመሪያ ዲግሪ እና ትራንስክሪፕት፤

፪/ በትምህርት ምዘና እና ፈተናዎች አገልግሎት ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት፤

፫/ የሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ከውጭ ሀገር የተገኘ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት በባለስልጣኑ የተመዘነ

፬/ የመጀመሪያ ዲግሪ መግቢያው ዲፕሎማ ከሆነ ፈቃድ ካለው ተቋም

***<u>educational credentials obtained through online education abroad:</u>***

Except for the visa requirements, not withstanding all the requirements indicated from article 10 to 15, the foreign online teaching institution should have institutional or program accreditation to offer online learning;

*17. **<u>Concerning Equivalence</u>***

1/ When professional nomenclature, rank descriptor and license are attached along with the educational or training credentials on which evaluation for equivalence is undertaken, the evaluation shall be made for the educational or training credential and for the level indicated thereto;

2/ The authority shall only give equivalence evaluation service for education and training credentials, the service is not available for any other credential such as equivalence performed abroad or professional license, different from educational and training credentials;

3/ Where the education or training credential submitted for evaluation is temporary certificate, the evaluation shall be values for six months till the original certificate is brought. Equivalence evaluation on the temporary certificate may be renewed for a second six months terms; such a renewal shall not be permitted for a third term

4/ Where foreigners whose native languages are different from English seek equivalence

Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education

የተገኘና ትክክለኛነቱ በፈቃድ ሰጪው አካል የተረጋገጠ ኦሪጅናል ዲፕሎማ እና ትራንስክሪፕት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፲፬. **<u>የሁለተኛ ዲግሪ ኖሯቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀጥሮ ለመስራት ወይም ለመማር የሚያገለግል ምዘና ለማሠራት</u>**

ከላይ በአንቀጽ ፲ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል

፩/ የሁለተኛ ዲግሪ እና ትራንስክሪፕት፤

፪/ የመጀመሪያ ዲግሪ የምስክር ወረቀት እና ትራንስክሪፕት

፫/ የመጀመሪያ ዲግሪው በሀገር ውስጥ ከሚገኝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተገኘ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሰረት በባለስልጣኑ የተረጋገጠ

፬/ የመጀመሪያ ዲግሪ ከውጭ ሀገር የተገኘ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት በባለስልጣኑ ሊመዘን ይገባዋል፡፡

፲፭.**<u>የሶስተኛ ዲግሪ ኖሯቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀጥሮ ለመስራት ወይም ለመማር የሚያገለግል ምዘና ለማሠራት</u>**

ከላይ በአንቀጽ ፲ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል

፩/ የሶስተኛ ዲግሪ እና ትራንስክሪፕት፤

፪/ የመመረቂያ ጽሁፍ የሰራ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፤

፫/ የሁለተኛ ዲግሪ እና ትራንስክሪፕት፤

evaluation certificate to qualify for a certain profession, they shall provide legal evidence proving their English language competence;

5/ Religious educational credentials shall not have equivalence evaluation service;

6/ Where the service seeker presented credentials in languages different from English, official English translation of the credential shall be attached from concerned Embassy or legal translation firms;

7/ Customers who had previously taken equivalence valuation have lost their equivalence document, they shall fulfill all the criteria and may take a replacement certificate;

8/ Where sufficient evidence is found about valuation certificate was issued to applicants through unfair or other means, the authority may revoke or cancel the valuation certificate issued;

9/ Where the equivalence valuation was issued to the applicant using a wrong evaluation, due correction shall be made by the authority which may issue a replacement certificate.

10/ Revocation or cancellation of equivalence certificate so revoked or cancelled shall be communicated and the original returned to the authority within one month;

**<u>Part Four</u>**

፬/ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ዲግሪው በሀገር ውስጥ ከሚገኝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተገኘ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሰረት በባለስልጣኑ የተረጋገጠ

፭/ የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪው ከውጭ ሀገር የተገኘ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሠረት በባለስልጣኑ የተመዘነ

፮/ በትምህርት ማስረጃው ላይ ከመመረቂያ ጽሁፍ ርዕስ በተጨማሪ የትምህርት መስኩ በግልጽ ካልተጠቀሰ ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

**፲፮. በበይነ-መረብ ከውጭ ሀገር የተገኘ የትምህርት ማስረጃ አቻ ግመታ ለማሰራት**

አቻ ግመታ ለማሰራት ከቪዛ ውጭ ከአንቀጽ 10 እስከ 15 ድረስ የተዘረዘሩት ማማሏት እንደተጠበቀ ሆኖ በውጭ ሀገር የሚገኘው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በበይነ መረብ መርሃ ግበር ለማስተማር የተቋም ወይም የትምህርት መስክ እውቅና ያለው መሆን ይገባዋል።

**፲፯. አቻ ግመታን በተመለከተ**

፩/ ለምዘና ከቀረበው የትምህርትና ስልጠና ማስረጃ ጋር የተያያዙ የሙያ መጠሪያ ስያሜ የማዕረግ ስያሜ እና የሙያ ፍቃድ ሲኖር ምዘናው የሚከናወነው ለትምህርት እና ስልጠናው ማስረጃ ወይም ደረጃው ብቻ ነው።

**Miscellaneous Provisions**

*18. **Grievance and Resolution Procedure***

Any person aggrieved with the actions and decisions of the service provider may file its grievance to the authority.

*19. **Inapplicable Laws***

Any directive, administrative decision and customary practice which is contrary to this particular directive shall not be applicble.

*20. **Amendment of the Directive***

The ministry of education may amend the directive at any time where it is deemed necessary.

*21.* **Effective date**

This directive shall be effective as of the date its registration with the ministry of justice and its uploading on the official website of the ministry of education.

**Addis Ababa, 2024**

**Berhanu Nega (Professor)**

**Minister, Minstry of Education of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**

፪/ ባለስልጣን መስሪያቤቱ የምዘና አገልግሎት የሚሰጠው ለትምህርት እና ስልጠና ማስረጃ ብቻ ሲሆን ከውጭ ሀገር የተሠጠ የአቻ ግምት ማስረጃ ወይም የሙያ ፍቃድ ወይም ሌላ ከትምህርት ወይም ስልጠና ማስረጃ ውጭ ያለ ማንኛውም ማስረጃ የምዘና አገልግሎት አይሰጠውም፡፡

፫/ የቀረበው የትምህርት ወይም ስልጠና ማስረጃ ጊዜያዊ ከሆነ ኦሪጂናሉ እስከሚቀርብ ድረስ ለ6 ወራት የሚያገለግል ጊዜአዊ የምዘና ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ ጊዜአዊ የምስክር ወረቀቱ ለ2ኛ ጊዜ ለ 6 ወራት ብቻ የሚያገለግል ዕድሳት ሊሰጠው ይችላል፤ ለ3ኛ ጊዜ ግን ዕድሳት አይፈቀድም፡፡

፬/ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ የተለየ ሌላ የውጭ ቋንቋ ተናጋሪ የውጭ ሀገር ዜጎች ለሙያ ፍቃድ ምዝገባ የሚያገለግል የምዘና ምስክር ወረቀት ሲፈልጉ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ክህሎት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡

፭/ የሀይማኖት ነክ የትምህርት ማስረጃ የምዘና አገልግሎት አይሰጣቸውም፡

፮/ አገልግሎት ፈላጊው ያቀረበው መረጃ ከእንግሊዝኛ ውጭ በሌላ ቋንቋ የተጻፈ ከሆነ በሚመለከተው ኤምባሲ ወይም ከህጋዊ ተርጓሚ ድርጅቶች ወደ

| | |
|---|---|
| እንግሊዝኛ ተተርጉሞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡<br>፯/ ባለጉዳዮች ከዚህ በፊት የምዘና አገልግሎት ተሰጥቷቸው ነገር ግን የምዘና ምስክር ወረቀቱ ቢጠፋባቸው ሁሉንም መስፈርት በድጋሚ አሟልተው ምትክ የምዘና ምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡<br>፰/ በተሳሳተ ውሳኔ ወይም በሌላ ባልተገባ ሁኔታ የምዘና ሰርተፊኬታ ለባለጉዳዮች የተሰጠ መሆኑ በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ ወይም ባልተገባ ሁኔታ የተሰጠ ምስክር ወረቀት አሰራሩ አስቀድሞ ባይኖር ምስክር ወረቀቱ አያሰጥም ሊያስብል የሚችል ከሆነ ባለስልጣኑ የምዘናውን ሰርተፊኬት የመሻር ወይም ውድቅ የማድረግ ስልጣን ይኖረዋል፡፡<br>፱/ የምዘና ሰርተፊኬቱ ለባለጉዳዩ የተሠጠው ከተሳሳተ ምዘና በመነጨ ውሳኔ ከሆነ ተገቢው ማስተካከያ ተደርጎ ምትክ የምስክር ወረቀት ለባለጉዳዩ ይሰጣል፡፡<br>፲/ የተሻረው ዋናው የምዘና ስረተፊኬት ከተሻረበት ቀን ጀምሮ ለባለጉዳዩ ወይም ለተወካዩ እንዲያውቀው ተደርጎ እና መልስ እንዲሰጥበት ይደረጋል፡፡ የተሰጠው መልስ ውሳኔውን የማያስቀይር ከሆነ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለባለስልጣኑ ተመላሽ መሆን አለበት፡፡ | |

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፰.. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት

በዚህ መመሪያ መሰረት አገልግሎት በሚሰጣቸው ማናቸውም ዉሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ለባለስልጣኑ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

### ፲፱.. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ የአስተዳደር ውሳኔ፣ የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም።

### ፳.. መመሪያውን ስለማሻሻል

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የትምህርት ሚኒስቴር መመሪያውን በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል።

### ፳፩. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በትምህርት ሚኒስትር ድረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ 2016 ዓ.ም**

**ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education